# ምርጫው የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ ነው

ክፍል ሁለት

ለሚ ዋቄ 11-27-14

*በዚሁ ርዕስ በቀረበ ክፍል አንድ ፅሁፍ ዘንድሮ ከሚካሄደው 5ኛ ዙር ምርጫ ጋር በተያያዘ የአውሮፓ ህብረት በምርጫው ዙሪያ እንቅስቃሴ ማድረግ መጀመሩን መነሻ በማድረግ የአውሮፓ ህብረት የምጫ ታዛቢ ቡድን በ1997 ዓ/ም የተካሄደው ምርጫ ላይ ያሳየውን አሳፋሪ ተግባርና የቡድኑ መሪ የነበሩት አና ጎሜዝ እስካሁንም በኢትዮጵያ ላይ የያዙትን አቋም ተመልክተን ነበር። የህብረቱ ታዛቢ ቡድን የተዛባ ድምዳሜ የያዘ ሪፖርት አውጥቶ ምርጫውን ተከተሎ ለተቀሰቀሰው ሁከት አሰተዋፀኦ ማድረጉንም አንስተን ነበር። ከአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ጋር የተያያዙ ቀሪ ጉዳዮችን በዚህ ክፍል ሁለት ፅሁፍ እንመለከታለን።*

እንግዲህ የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ምርጫ 97 ላይ ከታዛቢ ቡድን የማይጠበቅ ፀያፍ ድረጊት ቢፈፅምም፣ በ2002 ዓ/ም የተካሄደውን 4ኛ ዙር ምርጫ እንዲታዘበ ተጋብዞ እንደነበረ ይታወሳል።

በዚህ መሰረት የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን የ2002ቱን ምርጫ ታዝቧል። የዚህ ምርጫ ሂደትና የምርጫው እለት የነበረው ሁኔታ እንከን የለሽ ሰለነበረ የአውሮፓ ህብረት ታዛቢ ቡድን እነደለመደው ለመዘላበድ አልተመቸውም። ይሁን እንጂ ከወራት ቆየታ በኋላ ባወጣው ሪፖርት “ ምርጫው ዓለም አቀፍ መስፈርት አያሟላም፣ የምርጫው የፖለቲካ ምህዳር የፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩል አቅም የሚፎካከሩበት አልነበረም . . .” ብሏል።

“ዓለም አቀፍ የምርጫ መስፈርት” በሚል የገለፀው ተጨባጭነት የጎደለው በመሆኑ ምን ለማለት እንደፈለገ ለማንም የሚገባ አለነበረም። ምርጫው ላይ እንከን ሲፈልጉ የነበሩ ወገኖች ካልሆኑ የዚህ “ዓለም አቀፍ መስፈርት” በሚል የተገለፀ ሃሳብ ‘ገባኝ’ የሚል

አላጋጠመኝም። ምርጫው የተካሄደው ኢተዮጵያ ውስጥ ነው፤ ሂደቱ ትክክል ነበር ወይንስ አልነበረም? የታዛቢ ቡድኑ አስተያየት እዚህ ላይ ነው ማተኮር የነበረበት።
"ፓርቲዎች አኩለ የመፎካከር አቅም አልነበራቸውም" የሚለውም የታዛቢ ቡድኑ አስተያየትም ሆን ተብሎ ለማደናገር የተሰነዘረ፣ የምርጫው ወጤት ታዛቢ ቡደኑ ከሚፈልገው ጋር ባለመጣጣሙ የተደረገ ነው።

እርግጥ ነው ኢህአዴግ በተወዳደረባቸው፤ የትግራይ፣ የአማራ፣ የኦሮሚያና የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ብሄራዊ ክልላዊ መንግስታት ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እጅግ በሰፊ ልዩነት አሸነፏል። በአፋር፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ፣ የጋምቤላ ህዘቦች፣ ቤኒሻንጉል ጉምዝ እና ሃራሬ ክልላዊ መንግስታት ውስጥ ደግሞ የኢህአዴግ የአላማ ተጋሪና አጋር ድርጅቶቸ አሸንፈዋል። በዚህም ኢህአዴግ በተወዳደረባቸው ክልሎች በክልላዊ መንግስታት ምክር ቤት እና በፌደራል የህዝብ ተወካዮቸ ምክር ቤት ውስጥ አሸነፏል። ባልተወዳደረባቸው ክልሎች ደግሞ አጋር ድርጀቶቹ በማሸነፋቸው በፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ውስጥ ከነአጋር ድርጀቶቹ ከሁለት በስተቀር የተቀሩትን መቀመጫዎቸ መያዝ ችሏል። አንዱ በግል ተወዳደሪ ሲያዘ ሌላኛው ደግሞ በመድረክ ተወካይ ተያዘ።

ኢህአዴግ በሰፊ ልዩነት ያሸነፈው የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን እንዳለው፣ የፖለቲካ ምህዳሩ ለተቃዋሚዎች እንዳይመች ስለተደረገ ወይም ጠባብ ሰለነበረ አይደለም። የምርጫው ሂደት ይህን በትክክል ያረጋግጣል። ኢህአዴግና አጋሮቹ ድርጅቶች ተቃዋሚዎቹን በሰፊ ልዩነት ማሸነፍ የቻሉት የፖለቲካ ምህዳሩ ሰለጠበበ ሳይሆን፣ ተቃዋሚዎች በሰፊው የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ የመፎካከር አቅም የሌላቸው ደካማዎች ሆነው በመቅረባቸው እንዲሁም 'አይነ ገብ' ነን የሚሉት የተወሰኑት ፓርቲዎች የኢትዮጵያ ፖለቲካ መሰረት በሆነውና የህገመንግስቱም አምድ በሆነው የብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብትና ነፃነት ላይ ያላቸው አቋም በህዝቡ ተቀባይነት ስለሌለው ነው። ይህን ያደረገው መንግስት ወይም ገዢው ፓርቲ ኢህአዴገ አይደሉም።ራሳቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎቹ ናቸው።

‘አንጋፋ’ ነን የሚሉ የሃገሪቱ ተቃዋሚ ፓርቲዎቸ በ1997ቱ 3ኛ ዙረ ምርጫ ላይ በአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ጭምር እየታገዙ ባካሄዱት ህገመንግስታዊ ስርአቱን በሃይል የመናድ ሙከራ ማደረጋቸውና ሙከራው የተወው ጠባሳ፣ እንዲሁም ፓርቲዎቹ በውስጠ ዴሞክራሲ እጦረት እርስ በርስ መሻኮትና መወነጃጀል ዋና መገለጫቸው በመሆኑ የህዝብን አመኔታ አጥተዋል። ከዚህ በተጨማሪ ከተቃዋሚዎቹ መሃከለ በተለየ ‘አለን፣ አለን’ የሚሉት አንድ ሁለቱ የተለያዩ ብሄሮች፣ በሄረሰቦችና ህዘቦች የሚኖሩባትን ኢትዮጵያ በአሃዳዊ የመንግስት ስርአት የማስተዳደር የፖሊሲ አማራጭ ነው የያዙት። በዚህ ምክንያት የሕዝብን ድጋፍና አመኔታ ማግኘት አልቻሉም። ይህ በውስጥ ሹክቻ ከደረሰባቸው ድርጅታዊ አቅመደካማነት ጋር ተዳመሮ ከኢህአዴግ ጋር  የመፎካከር አቅማቸው እጅግ  ሲበዛ ደካማ እንዲሆን አደረገ።

በሌላ በኩል ኢህአዴግ ከምርጫ 97 በፊት የጀመራቸው በህዝቡ ሕይወት ላይ ተጨባጭ መሻሻል ያመጡ ስራዎች ፍሬ አፍርተው እውነተኛ ማንነቱ በመገለፁ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ኢህአዴግ ቀደም ሲል “ማንነቴን ስራዬ የናገራል” በሚል መተማመን ችላ ብሎት የነበረው የህዝብ ግንኙነት ስራ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራቱ እውነተኛ ማንነቱን ለህዝብ በማሳወቁ ተቃዋሚዎቹ በኢህአዴገ ፊት እጅግ ትናንሽ እንዲሆኑ አድርጓል።

ይህ በተቃዋሚዎቹ በራሳቸው ድክመት የተፈጠረ በሰፊ የፖለቲከ ምህዳር ውስጥ የመፎካከር አቅመቢስነት እንደስርአቱ ችግር ተደረጎ መቅረብ አለነበረበትም። ቀድሞውንም ገለልተኛ ያልነበረው የአወሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ግን፣ የምርጫው ውጤት፣ እንዲሆን ከሚፈልገው ጋር ባለመጣጣሙ ደስተኛ ስላልነበረ ምርጫውን ለማጣጣል በማሰብ ነው “የፖለቲካ ምህዳሩ ተመጣጣኝ ፉክክር ያልተደረገበት ነበር” የሚል የማደናገሪያ ምስክርነት የሰጠው።

የህብረቱ ታዛቢ ቡድን በተፎካካሪዎች መሃከል የነበረውን ከላይ የተገለፀ እውነታ “አያውቀውም” ብሎ መገመት ስህተትነቱ ያይላል። ከዚህ ይልቅ ይህን እውነታ መቀበል አለመፈለጉ ትክክል ነው። የህብረቱ ታዛቢ ቡድን እንዲያሸንፉ ይፈልግ የነበረው ደካማ ተቃዋሚዎች የተሸነፉት በመንግስት እና/ ወይም በገዢው ፓርቲ ተፅአኖ ነው የሚል እይታ እንዲፈጠር  የፈልግ ነበረ።

የህብረቱ ታዛቢ ቡድን ይህን ከቡደኑ ፍላጎት የመነጨ አቋም ትክክለኛነት ያረጋግጥልኛል ያለውን አንድ ጉዳይ በትዝብት ሪፖርቱ ላይ ጠቀሶ እነደነበረ ይታወሳል። ይህም መድረክ/አንድነትን በመወከል በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 6 ተወዳድረው ያሸነፉትን የተከበሩ አቶ ግርማ ሰይፉ መነሻ ያደረገ ነው።

ታዛቢ ቡደኑ ባወጣው ሪፖርት "አቶ ግርማ ሰይፉ ማሸነፍ የቻሉት የተወዳደሩበት ወረዳ 6 በንግድ ስራ የሚተዳደሩና ከመንግስት ተፅአኖ ነፃ የሆኑ ነዋሪዎች የሚኖሩበት በመሆኑ ነው" ብሎ ነበር። ሌላው አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ ኢህአዴግን የመረጠው በተፅእኖ ነው የሚለውን ያረጋግጥልኛል በሚል ነው ይህን ያለው። ወረዳ 6 በመርካቶ አቅራቢያ የሚገኝ በመሆኑ በርካታ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች የሚኖሩበት መሆኑ እወነት ቢሆንም ሙሉ በሙሉ "የንግዱ ማህበረሰብ መኖሪያ ነው" ሊባል የሚችል ግን  አይደለም።

የወረዳ 6 እንደማንኛውም የአዲሰ አበባ አካባቢ ከፍተኛ፣ መካከለኛና ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚኖሩበት ከሌላ አካባቢ ያለተለየ የኑሮ፣ የትምህርት ደረጃና ስነልቦና ያለው ሕብረተሰብ የሚኖርበት አካባቢ ነው። የወረዳ 6 ህዝብ አቶ ግርማ ሰይፉን የመረጠው፣ ተወለደው ያደጉበት አካባቢ በመሆኑ፣ በትምህርት ብቃታቸው፣ በሰነምግባራቸውና በማህበራዊ ተሳተፏቸው እነደ ግለሰብ 'ከተፎካካሪያቸው የተሻሉ ናቸው፣ አውቃቸዋለሁ" ብሎ ሰላመነ ብቻ ነው። የአውሮፓ ህብረት ግን ይህን አያውቅም፣ ወይም ማወቅ አይፈልግም። በምርጫው  "ኢህአዴግ መሸነፍ ነበረበት" በሚል አስቀድሞ የያዘውን አቋም ትክክለኝነት ያረጋግጣል በሎ ሰላሰበ ብቻ እውነታውን ከማንም በላይ ለምናውቀው የአዲሰ አበባ ነዋሪዎቸ ጭምር ውሸት አወራልን።

በሌላ በኩለ እርግጥ  በተቀጣሪነትም ሆነ በሌላ ትስስር የገቢ ምንጫቸው ከመንግስት ፍፁም ነፃ የሆኑ በከፍተኛ ንግድና አገልግሎት ስራዎች የሚተዳደሩ፣ በኢትዮጵያ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሃገራትም መለኪያ ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ነዋሪዎች በአብዛኛው የተሰባሰቡበት የአዲሰ አበባ ከተማ አካባቢ አለ። ለምሳሌ በቦሌ ክፍለ ከተማ ውስጥ የሚገኙ  ወረዳዎች። በዚህ አካባቢ የሚኖሩ ዜጎች ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ በውጭ ሃገራት የመኖር እድል ያላቸውም ናቸው።

ታዲያ በዚህ አካባቢ ባሉ ወረዳዎች ኢህአዴግ እነደሌሎች አካባቢዎች ሁሉ በሰፊ ልዩነት ነበር ያሸነፈው። የህ ተጨባጭ እውነታ፣ የ2002ቱን ምርጫ የታዘበው የአውሮፓ ህብረት የታዛቢ ቡድን "መንግስት በምራጩ ላይ ተፅእኖ አሳድሯል" በሚል መነው አቶ ግርማ ሰይፉ የተመረጡበትን አካባቢ ከተፅእኖው ነፃ ነው በሚል የሰጠው ትንታኔ ፍፁም መሰረተ ቢስና አሳፋሪ መሆኑን ያሳያል።

እንግዲህ ከዚህ አኳያ ስንመለከተው የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ዘንድሮ ግንቦት ላይ የሚካሄደውን 5ኛ ዙር ሃገራዊና ክልላዊ ምርጫ ለመታዘብ ባይጋበዝ ተገቢና ትክክለኛ ነው።

የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮቸ ጽህፈት ቤት ምኒስትር አቶ ሬድዋን ሁሴን በቅርቡ በሃገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን በተመለከተ የቀረበላቸውን ጥያቄ መነሻ በማድረግ የሰጡት ማብራሪያ በአውሮፓ ህብረትና መሰል የውጭ የምርጫ ታዛቢ ቡድኖች ዙሪያ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በግልፅ አሳይቷል። ለዚህ ጽሁፍ ዓላማ ጠቃሚ ሆኖ ስላገኘሁት አቶ ሬድዋን በጉዳዩ ዙሪያ የሰጡትን ማብራሪያ እጠቅሰዋለሁ።

*የአቶ ሬድዋን ማብራሪያ፤ "የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን በተመለከተ የኢትዮጵያ መንግስት ከአሁን በፊትም ተመሳሳይ አቋም ነው ያለው። ይህም 'የታዛቢዎች ሚና ምርጫን መታዘብ ነው' የሚል ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ ተስማምተን የምናስቀምጠው አቋም አለ። በዚህ ዙሪያ ያለው ዋና ጉዳይ 'የምናካሂደው ምርጫ የእኛን ዴሞክራሲ፣ የእኛን ምርጫ ምን ያህል ከፍታ ላይ ያስቀመጠዋል' የሚል ነው።*

*ሕዝባችን በዚህ ምርጫ ላይ ምን ያህል በተጨባጭ መረጃ ላይ የተመሰረተ አቋም እንዲይዝ እናደርጋለን? እዚህ ላይ በመንተራስ በራሱ ነፃ ፍላጎት የሚፈልገውን አካል መምረጥ ይችላል የሚለ ነው።*

ምርጫው ከእኛ ጥቅም ነው የሚነሳው፤ ከእኛ እመነት ነው የሚነሳው፤ በእኛ ወሳኝነት ነው የሚፈፀመው። የውጭ ታዛቢዎች በምርጫው ላይ ያላቸው ድርሻ ሁለተኛ፣ ሶስተኛም . . . አይደለም። ራቅ ያለ ድርሻ ነው ያላቸው። እርግጥ ለራሳቸው እርካታ የሚታዘቡበት ምክንያት ይኖራቸዋል።

ከዚህ ቀደም አንዳንዶቹ ምርጫን ለመታዘብ በመጡበት ወቅት ታዝበው አለመሄድ ብቻ ሳይሆን፣ አሁንም ከሃገራችን አንዳንድ ተቃዋሚዎች የበለጠ ባለቤት ነን የሚሉ አሉ። እንዲህ አይነት ታዛቢ፣ ታዛቢ አይደለም። መዘውሩን ይዞ ሃገሪቱን በራሱ ቅኝት መምራት የሚፈልግ ነው። "የበግ ለምድ የለበሰ ቀበሮ" እንዲሉ።

የታዛቢነት መመዘኛዎችን አሟልቶ፣ በእርግጥም ስራው መታዘብ ብቻ መሆኑን አውቆ፣ ከፈራጅነት ወጣ ብሎ ሂደቱን ብቻ ታዝቦ መናገር የሚችል ታዛቢ ሊኖር ይችላል። ዋናው ነገር ማንም ታዛቢ መጣ ቀረ በምርጫው ሂደት ላይ ምንም ተፅእኖ የማይኖረው መሆኑ ነው።

የምርጫው ባለቤት መሆናችንን አውቆ፣ የሚወስነው ሕዝቡ መሆኑን ተቀብሎ፤አስቀድሞ ውጤት ጠብቆና አማትሮ ሳይሆን የምርጫ ሂደት አይቶ የሚመሰክር ታዛቢ ነው የሚያስፈልገው።

ከዚህ ቀደም ያየናቸው አንዳንድ ታዛቢዎች ግን ውጤት አስልተው ነበር የመጡት። 'ይህን ያህል ተቃዋሚ ምርጫው ላይ ከገባ ምርጫው ጥሩ ይሆናል፤ ይህን ያህል መቀመጫ በተቃዋሚዎች ካልተያዘ ምርጫው ዋጋ የለውም።' የሚል ውሳኔ ይዘው ነበር የመጡት። ስለዚህ 'ሂደቱ ጥሩ ነበር፣ ውጤቱ ግን ደስ አይልም' በለው ነው የሄዱት። በምርጫ ላይ፣ ሂደቱ ነው ደስ ይላል ወይም ደስ አይልም መባል ያለበት። ውጤቱ የባለቤቶቹ ነው።

እናም በመጪው ምርጫ 'የምርጫው ውጤት እንዲህ መሆን አለበት' በለው አስቀደመው ወስነው የሚታዘቡ አካላት እንዲንነማለሉ የሚፈቀድላቸው አይመስለኝም።" የሚል ነበር።

እንግዲህ ከዚህ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ምኒስትር አቶ ሬድዋን ሁሴን ከሰጡት ማብራሪያ አኳያ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ከነበረው ተጨባጭ እውነታ አኳያ ስንመለከተው፣ የመጪው ምርጫ ወጤት ምን መሆን እንዳለበት አስቀድሞ አቋም ይዞ በመምጣትና፣ ምርጫውን ከሂደቱ ሳይሆን አስቀድሞ ከያዘው አቋም አኳያ መዝኖ ውኆንብር በመንዛት የሚታወቀው የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ላይጋበዝ ይችል የሆናል። የአውሮፓ ህብረት ምርጫውን መታዘቡ ከዚህ ቀደመ እንደታየው የሃገሪቱን የዴሞክራሲ ሂደት ለማቀንጨር ከመሞከር ያለፈ ፋይዳ አለወ በሎ መናገር አይቻልም። ይህ በተግባር ታይቷል።

ምርጫውን ለራሱ ከአይዲዮሎጂ ልዩነት ለመነጨ ፍላጎቱ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚፈልገው የአውሮፓ ህብረት "ምርጫውን ለመታዘብ ይጋበዛል" ተብሎ ባይጠበቅም፣ በክፍል አንድ ፅሁፍ ላይ እንደጠቀስኩት ከወዲሁ ምርጫውን መነሻ በማደረግ በየክልሉ ዲፕሎማቶቹን ልኮ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ የሆነው የመንግስት ስልጣን በውክልና የሚሰጥበት የምርጫ ጉዳይ ውስጥ ጣልቃ ለመግባት እየተነቀዠቀዠ ይገኛል። ይህን የኢትዮጵያ ህዝብ ልብ ሊለው ይገባል።

የአውሮፓ ህብረት አባል ሃገራት የልማት አጋሮቻችን መሆናቸው ባይዘነጋም፣ የልማት አጋርነት በጋራ የበለፀገች ዓለም በመፍጠር ይህ ብልፅግና ከሚያሰከትለው አስተማማኝ ሰላምና ሰፊ የገበያ ልውውጥ ዘላቂ የጋራ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ መርህ ላይ መመስረት ይኖርበታል እነጂ፣ አንዱ ሃገር ህዝብ ለሌላው ሉዓላዊቱንና ነፃነቱን አሳልፎ ሰጥቶ ጥገኛ የሚሆነበት ሁኔታን መፍጠረ አይኖርበትም። የኢትዮጵያ ህዝብና ሕዝብ በውክልና ስልጣን የሰጠው የኢፌዴሪ መንግስት የልማት አጋርነት ግንኙነትን ከዚህ አኳያ ነው የሚገነዘቡት። ስለዚህ የአወሮፓ ህብረት በተለይ ምርጫን አስታኮ የሚካናወናቸው አንዳንድ እንቅስቃሴዎች ለነፃነቱና ለሉዓላዊነቱ ቀናኢ ለሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ የሚመቹ እንዳልሆኑ ከወዲሁ ተገንዝቦ አካሄዱን ቢያቃና መልካም ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ እነኳን አሁን ባለንበት ዘመን፣ ሁሉም የአፍሪካና የኢስያ ሃገራት በአውሮፓውያን ቅኝ ግዛት ስር ወድቀው በነበረበተ 19ኛውና 20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ እንኳን ለምእራባውያን ቅኝ ገዢዎች ያልተንበረከከ ህዝብ ነው። የቅኝ

ገገርዎችን ወረራ ከመመከት ባሻገረ በተለያየ መንገድ በዘረጓቸው የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ወጥመድም አልተጠለፈም። ይህ በአጋጣሚ የሆነ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ ለነፃነቱና ሉዓላዊነቱ ባለው ቀናኢነት በመስዋእትነት ያረጋገጠው ነው። ይህን አውሮፓውያኑም ጠንቅቀው ያወቁታል። ይህ ነባር የህዝበ ስሜት በአዲሱ ትውልድም ውስጥ አለ።

ከምእራባውያን ጋር 'ጀብ ጀብ' የሚሉትን አንዳንድ ልሂቃንና ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን ህዝቡ እንደባንዳ ነው የሚመለከታቸው። የኢትዮጵያ ህዝብ ባንዳ ምን እንደሆነ ያውቃል፤ በተግባር። 'ለመሰልጠንና ለመበልፀግ በቅኝ ግዛት ስር መውደቅ ነበረብን' የሚሉ የኢትዮጵያን ቀደምት ስልጣኔ ዋጋ የማያወቁ፣ ኢትዮጵያ በህዳሴ አብዮት ዳግም የስልጣኔ ማማ ላይ ልትቀመጥ እንደማትችል የማይረዱ በቁማቸው የሞቱ ልሂቃን መኖራቸው የታወቃል። እነዚህ ልሂቃን፣ ምእራባውያንን ሁሉን ማድረግ የሚችሉ እነደአምላክ ምሉዕ በኩለሄ አድረገው ነው የሚወስዷቸው። እነዚህ ልሂቃን ለኢትዮጵያ ህዝብ - በሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዋጋ አይሰጡም። ምእራባውያኑ ወደስልጣን የሚያወጧቸው አንጋሽ ሆነው ነው የሚታዩዋቸው።

ይህ ግን በኢትዮጲያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ ነች። ምእራባውያን የአወሮፓ ሀገራትም ሆኖ አንጋሽ አድርገው የሚመለከታቸው ባንዳዎች ይህን ተገንዝበው ሰልፋቸውን የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች ከሆኑ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ጋር ማስተካከል አለባቸው። የህዝብ የመንግስት ስልጣን ምንጭና ባለቤትነት መገለጫ የሆነው መጪው ምርጫም የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያን ብቻ መሆኑን ምእራባውያኑና ባንዳዎቹ ሊያስታውሱ ይገባል።